# ወደ ቤተ-መጻፍት በደህና ምጡ!

ሁላቸው በየስትሪክላንድና በህልሲንግላንድ ያሉት ህዝባውያን ቤተ-መጻህፍቶች የስራ ትብብር ኣላቸው። HelGe-biblioteken ተብለው ደግሞ ይጠራሉ።

## የመዋሻ ካርድና የመዋስ ጊዜ

መጽሃፍ ለመዋስ/ለመበደር፡ የመዋሻ ካርድና ፒን-ኮድ ያስፈልግዎታል። የመዋሻ ካርድዎ በሁላቸው የHelGe-biblioteken ሊያገለግልዎት ይችላል። በያዙት ካርድ መጻህፍቶች፣ የኣለክትሮኒክ መጻህፍቶች፣ ፊልሞች፣ ጋዜጦች፣ የቋንቋ ኰርሶች፣ በድምጽ የተቀዱ መጻህፍቶችና ሌላ ሊዋሱ ይችላሉ። በተባሉት ቤተ-መጻህፍቶች፡ እንደፈለጉ መዋስ፣ መመለስ፣ ማዘዝና ወረፋ መያዝ አይችላሉ።

የብድሩ ጊዜ እርዝማኔ በሚበደሩት ሚድያ መሰረት ይለያያል። መጻፍቶች ኣብዛኛው ጊዜ ላራት ሳምንቶች ያህል ጊዜ ሊዋሱ ይችላሉ። በተለፎን መልእክት (አስ-አም-አስ) እና በኢ-መይል፡ የብድሩ ጊዜ ሊያልቅ ጥቂት ቀኖች ኣስቀድሞ ማስታወሻ
ይላክልዎታል። ሁሉ ጊዜ የብድሩ ደረሰኝ መያዝ ኣለብዎት!

የመበደሪያው ካርድ በጣም ኣስፈላጊ የሆነ ሰነድ (ዶኩመንት) ነው። በካርድዎ የሚዋሱዋቸው ሚድያዎች በሃላፊነት የሚጠየቁት እርስዎ ነዎት። ካርዱ የጠፋብዎ እንደሆነ፣ በቶሎ ለቤተ-መጻህፍቶቹ ማስታወቅ ኣለብዎት። ምክንያቱም ሌላ ሰው ኣግኝቶ እንዳይጠቀምበት ለመከላከል ነው።

6 ዓመት ዕድሜ የሞላቸው ልጆች የገዛ ራሳቸው የመዋሻ ካርድ ልይዙ ይችላሉ። የልጁ ወላጆች ወይም ኣሳዳጊው ሞግዚት፡ ልጁ 18 ዓመት ዕድሜ ስካልሞላው ድረስ፡ በሚዋሳቸው ነገሮች ላይ ሃላፊነት ይሸከማሉ።

## ኣብዛኞው በነጻ ነው ሁሉም ግን ኣይደለም

በHelGe-biblioteken ለመዋስ በነጻ ነው።ግን የተዋሱት ሚድያ በጊዜ ሳይመልሱ ቢቀሩ፡ በየቀኑ ለያንዳንዱ ሚድያ፡ ኣንድ ክሩና ይከፍላሉ። ኣንዳንዶቹ ቤተ-መጻህፍቶች የቲቪ ማዝናኛ ያውሳሉ። የተዋሱት የቲቪ ማዝናኛ በጊዜ ያልመለሱ እንደሆኑ፡ 10፥-ክሩኑር በቀን ይከፍላሉ። የሚከፈለው ዕዳ 100፥-ክሩኑር ወይም ከ ዛም በላይ ከሆነ፡ ካርድዎ እንደማይሰራ ይደረጋል። ይኸ ማለት ደግሞ ዕዳዎ ከ100፥-ክሩኑር በታች እስካልወረደ ድረስ ለመዋስ ኣይችሉም ማለት ነው።

## የተሰበረ፣ የተበላሸ ወይ የጠፋ እንደሆነ

የተዋሱት ሚድያ ካበላሹ ወይም ካጠፉ እታች እንደተመለከተው ይከፍላሉ፣ የተበላሸው ወይም የጠፋው ነገር ዋጋው ውድ የሆነ እንደሆነ፣ የሚከፈለው ገንዘብ ሊለያይ እንደሚችል ማስተዋል ኣለብዎት።

| | |
|---|---|
| የትላልቆች መጻህፍቶችና በድምጽ የተቀዱ መጻህፍቶች | 300kr |
| የልጆች መጻህፍቶችና በድምጽ የተቀዱ መጻህፍቶች | 200kr |
| የሙዚቃ ሲዲ | 200kr |
| የልጆች ሲዲ | 150kr |
| ጋዜጣ | 50kr |
| ፊልምና የቲቪ ማዝናኛ | 700kr |
| ቋንቋና ሲዲ-ሮም | 500kr |
| ደይዚ የንግግር መጽሃፍ | 150kr |
| መዋሻ/መበደርያ ካርድ | 20kr |

እዚህ ገብተው መጽሃፍ መፈለግና ማንበብ ይችላሉ www.helgebiblioteken.se